# እግዚአብሔር ለምን ሰይጣንን ፈጠረው? ስለፈጠረውስ ተሳስቷል ወይ?

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

አዎ! እግዚአብሔር ነው ሰይጣንን የፈጠረው፡፡ ከእግዚአብሔር ውጪ ሌላ ፈጣሪ የለምና፡፡ እግዚአብሔር ብለን ስንል መጀመሪያ ስላልነበረው መጨረሻም ስለማይኖረው ወይም መጀመሪያውም መጨረሻውም አልፋና ዖሜጋ ስለሆነው ኢሳ. 48፤12 ራእ. 21፤6,22፤13 ስለሁሉም ነገር ፈጣሪ ማውራታችን ነው፡፡ እግዚአብሔር መጀመሪያ ካለው አስጀማሪም አለው ማለት ነው፡፡ አስጀማሪ ካለው ደግሞ ተፈጣሪ እንጅ ፈጣሪ አይደለምና ሌላ ፈጣሪ ፍለጋ ልንሔድ ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ፈጣሪ እንጅ ተፈጣሪ ስላልሆነ መጀመሪያ አልነበረውም መጨረሻም የለውም፡፡ መጀመሪያውም መጨረሻውም እሱ ነው፡፡ እናም ስለ እግዚአብሔር ስናወራ እንደሰው ልንረዳቸው የማንችላቸው ከሰው አእምሮና የመረዳት አቅም በላይ የሆኑ በርካታ ነገሮች መኖራቸውን መረዳት ግድ ይላል፡፡

እግዚአብሔር የዚህ ሁሉ የምናየውና የማናየው የምናውቀውና የማናውቀው ድንቅና ምሥጢራዊ ፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ መሆኑን ልብ ካልን እንዲሁም ስለፍጥረቶቹ የምናውቀውና ልናውቀውም የቻልነው እጅግ ኢምንት እንደሆነ፤ የማናውቀው ልናውቀውም ያልቻልነውና የማንችለው እጅግ ብዙ ነገር እንዳለ ካወቅን ስለፈጣሪ ብዙ ወይም ሁሉንም ነገር ለማወቅ መሻት መፈለግ መሞከር እጅግ የዋህነት ወይም ጅልነት መሆኑን እንድንረዳ የሚያስገድደን ይመስለኛል፡፡

እግዚአብሔር በዓይን የሚታዩትንና የማይታዩትንም፣ የቅርቡንም የሩቁንም፣ ረቂቁንም ግዙፉንም፣ ግልጹንም ስውሩንም፤ መልካሙንም መጥፎውንም፣ ተመሳሳዩንም ተቃራኒውንም ሁሉንም ፍጥረታት የፈጠረ እሱ ነው "ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም ሁሉ አንዳችስ እንኳ ያለ እሱ አልሆነም" ዮሐ.1፤3፡፡ "እሽ መልካም መልካሙንስ ይሁን መጥፎ መጥፎውንና ተቃራኒ ተቃራኒውን ግን ለምን ፈጠረው?" የሚል ጥያቄ ይነሣል ወደ ኋላ እናየዋለን፡፡

እናም ሰይጣንን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሰይጣንን ሲፈጥረው ሰይጣን አድርጎ ማለትም በክፉ ግብሩ አልነበረም የፈጠረው፡፡ ቅዱስ መልአክ አድርጎ ነበር የፈጠረው ከመልአክም ሳጥናኤል ብሎ የመላእክት ሁሉ አለቃ አድርጎ፡፡ እንደ ሁሉም ቅዱሳን መላእክት ሁሉ "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" እያለ ምስጋናው ምግብ ሆኗቸው እንደሚኖሩት ቅዱሳን መላእክት ፈጣሪን እያመሰገነ እንዲኖር ነበር የተፈጠረው፡፡ ነገር ግን ገና በመጀመሪያዋ ቀን በትዕቢት ያልተገባውን በመፈለጉ በፈተና ወደቀና ከቅዱስ መልአክነት ወደ ሰይጣንነት (ክፉነት) እራሱን ቀየረ፡፡ ክብሩን ብርሃኑን አጣ ጨለማን ለበሰ እራሱን ብቻ ሳይሆን በሐሰተኛ ምክሩ ያሳሳታቸውን አንድ ነገድ ይዞ ጠፋ ወደ ጥልቁ ወደ ጨለማው ወደቀ፡፡ ኢሳ. 14፤12-20, 1 ኛ ጢሞ.3፤6-7

እዚህ ላይ “ሰይጣን ክብሩን አጣ ብርሃኑን ተገፈፈ ጨለማ ለበሰ” ሲባል ይሄንን አባባል ጥቁሮች እኛን ለማጥቃት በነጮች የተፈጠረ አባባል ነው በማለት ይቃወሙታል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጆች ምንጭ በሃይማኖትም ሆነ በሳይንስ (በመጣቅ) አንድ መሆኑ ከታወቀና የቆዳ መንጣትና መጥቆር መንስኤው የአየር ንብረት መሆኑ ግልጽ ከሆነ ጥቁር ቀለም ወይም ጨለማ ከአስፈሪ ግርማው የተነሣ የአንዳች ክፉ ነገር መገለጫ በሆነ ቁጥር የጥቁር ዘር ለብቻው የተፈጠረ ይመስል “እኛን ለማጥቃት ነው!” እያልን እኛ አፍሪካዊያን መሸማቀቅ አይኖርብንም ሆን ብለው ለማጥቃት አስበው ቢናገሩትም ጭምር፡፡

እኛ የቆዳ ቀለማችን ጥቁር ስለሆነ እንድንሸማቀቅ ከተፈለገ ጥቁር ጸጉርና ጥቁር የዓይን ብሌን ያላቸው ነጮች ቢጫዎችና ቀዮችም መሸማቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ያንን ጥቁር ጸጉርና የዓይን ብሌናቸውን መጥላት አለባቸው ማለት ነው፡፡ ከልብስ ጀምሮ ምግቡንም መጠጡንም ጥቁር የሆነን ነገር ሁሉ ከራሳቸው ማራቅ ማስወገድ ሊኖርባቸው ነው ማለት ነው፡፡

ነገር ግን እነሱ ይሄንን ሲያደርጉ ወይም ሲሸማቀቁ አይታዩም፡፡ ጥቁር ጥቁር ነገር እንዳላቸው እንደነሱ ሁሉ የጸጉርና የዓይንና የቆዳ ጥቁረት ያለን እኛ ደግሞ “ሰይጣን ክብሩ ብርሃኑ ተገፎ ጨለማ ለበሰ” የሚለው ጉዳይ ከእኛ ጋር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ በመረዳት ቅድስና በሥራ እንጅ በቆዳ መንጣትና መጥቆር አይደለምና በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በሌሎቹ የቤተክርስቲያን መጻሕፍተ ቅዱሳት ጥቁር ቅዱሳን እንዳሉ ግልጥና የታወቀም ነውና ጥቁርነታችንን የእርኩስነት የሰይጣንነት መለያ አድርገን በመውሰድና በመጥላት ከሙብገን ከሙብከንከን መቆጠብ ይኖርብናል፡፡

ጨለማን በመፍራታችን እንደጠላነውና ጥቁር ቀለምም በአጋጣሚ ጨለማን በመምሰሉ የሚጠላበት ጎን ቢኖረውም ከሌሎች ቀለማት ሁሉ በበለጠ ጥቁር ቀለም የሚወደድበት የሚፈለግበት ዓይነት አጋጣሚ የራሱ ውበትና ግርማ ያለበት ሁኔታ ደግሞ አለና ነገሩን በአንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ጥቁርነት ሁሉም ቦታ ተፈላጊ እንዳለመሆኑ ሁሉ ነጭነትም ሁሉም ቦታ ተፈላጊ አይደለም፡፡ ጥቁር ቢሆን የምንጠላው ነገር እንዳለ ሁሉ ነጭ ቢሆንም የምንጠላው ነገር አለ፡፡

ብርሃን የጥሩ የክብር ጨለማ የክፉ ክብርን የመገፈፍ ተምሳሌት ሆኖ መወሰዱ ከዕለት ተዕለት ኑሯችንና ከሰው የመሆን ሥነልቡናችን አንጻር በጨለማ ውስጥ ምን እንዳለ ካለማወቃችን የተነሣ ምንም ነገር የሌለ ሆኖም እንኳ ጨለማን ከመፍራታችንና ከመጥላታችን በብርሃን ደግሞ ሁሉም ነገር ግልጥ ሆኖ ከመታየቱ የተነሣ የሚያስፈራ ነገር ባለመኖሩ ብርሃንን ከመውደዳችን አንጻር ብቻ የተሰጠ ተምሳሌትነት ነው፡፡

ጨለማን የሚጠላውና የሚፈራው ነጮቹ ብቻ ሳይሆኑ እኛን ጥቁሮቹን ጨምሮ ሁሉንም የሰው ዘሮች ነውና፡፡ በመሆኑም ሰይጣን ሲሳል ጨለማን ለብሶ ወይም ጠቁሮ መሳሉ እኛን ለማከፋፋት ለማጥቃት ነው እያልን ልንተረጉም አይገባም፡፡ እንዲህ እያሉ ሊያሸማቅቁን የሚሞክሩ ነጮች ካሉ በአላዋቂነታቸው ታዝበናቸው ንቀናቸው ከማለፍ ውጭ ሙብገንና ሙብሸቁ እራሱ አላዋቂነት ነው፡፡ ሰይጣን ጨለማ ለብሶ ወይም ጠቁሮ መሳሉ ክብሩን ብርሃኑን እንዳጣ ለማመልከት ብቻ ነው፡፡ ጥቁር ተደርጎ መገለጡ ያጋጣሚ የጨለማና የጥቁር ቀለም መመሳሰል ጉዳይ እንጅ የዓይነት

አንድነት ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲያ ቢሆን ኖሮ የጥቁር ቅዱስ ወይም ጻድቅ የነጭ ደግሞ እርኩስ ወይም ኃጥእ ባልነበረ፡፡ በመሆኑም ነገሩን ወደሌላ እያዞርን ባንቸገር መልካም ነው፡፡

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስና እግዚአብሔር ሰይጣንን የመላእክት አለቃ አድርጎ ቢፈጥረውም ሰይጣን ግን ያልተገባውን በመሻቱ በማመፁ በራሱ ጥፋት ወደቀ ሲባል አንድ ጥያቄ ይነሣ ይሆናል "እሺ እሱስ ይሁን ሰይጣን የማይገባውን የራሱ ያልሆነውን የእግዚአብሔርነትን የፈጣሪነትን ክብር ሽቶ፤ ፈጣሪ ሳይሆን ፈጣሪ ነኝ በማለቱ ቢወድቅም ወድቆም ከሙቶው ነገደ መላእክት ያሳሳታቸውን አንዱን ነገድ ይዞ ወደቀ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነውና ነገሮች ከመሆናቸው ከመፈጸማቸው በፊት ገና ሳይሆን ሳይፈጸም ያውቃልና ሰይጣን እንዲህ ሆኖ እንደሚስት ስቶም እንደሚያስትና ለእርኩሰት ለጥፋት ለፈተና ለኃጢአት ሁሉ አስተማሪዋ አባቷ እንደሚሆን አስቀድሞ እያወቀ ለምን ፈጠረው?" መባሉ አይቀርም፡፡ አዎ በእርግጥም መነሣት ያለበት አግባብነትም ያለው መመለስም ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ ነው፡፡ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በዚህ መሠረታዊ ጥያቄና በዙሪያው ስለሚሽከረከሩ ተጓዳኝ ጥያቄዎች አንሥተን እንወያያለን፡፡

እንግዲህ ነገሩ እንዲህ ነው፡- እርግጥ ነው እግዚአብሔር ፈጣሪ ነውና ነገሮችም ከመፈጸማቸው በፊት ሳይፈጸሙ ገና ያውቃል፡፡ "እግዚአብሔር የመላእክት አለቃ አድርጎ የሾመው ሳጥናኤል እንደሚስትና ስቶም እንደሚያስት እያወቀ ለምን ፈጠረው?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ የእግዚአብሔርን ፍጹም ቅንነት፣ ፍጹም ፍትሐዊነት፣ ለፍጥረቱ ሙሉ መብትና ነጻነት ሰጭነቱንና የሰጠውንም መብትና ነጻነት አክባሪነቱን (perfectly democrat) እንዲሁም እንከን ወቀሳ የሌለበት ፍጹም የሆነ አምላክነቱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ምላሹም፡-

እግዚአብሔር ሁሉንም የፈጠረ እሱ ቢሆንም የፈጠራቸውን ፍጥረታት እንበል ለምሳሌ አስቀድሞ መላእክትን በኋላም የሰው ልጆችን "ፈጣሪያቹህ እኔ ነኝና በግድ እኔን አምልኩ ለእኔ ተገዙ!" ብሎ አስገድዶ በግድ እንዲያመልኩት ፈጽሞ ስለማይፈልግና ፈቃዱም ስላልሆነ ነው "በፊታቹህ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥኩ እኔ ዛሬ ሰማያትንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ!" ዘዳ. 30፤19

"እጅህን በመረጥከው ትጨምር ዘንድ እነሆ እሳትና ውኃን አኖረልህ" መጽ. ሲራክ. 15፤16 በማለት እሳቱን (መተላለፍን)፣ ሞትን፣ መርገምን ብንመርጥ የሚያገኘንን ዘለዓለማዊ ፍዳ፤ ውኃውን መረከቱን ሕይወትን ብንመርጥ የምናገኘውን ዘለዓለማዊ ተድላ ደስታ ሕይወት በሚገባ ከማሳወቅ ጋር ሁሉንም አማራጮች ክፍት አድርጎ በማቅረብ ፍጹም ነጻ ፈቃድና መብትን ሰጥቶ በነጻነት ባለን ሙሉ መብት ሕይወት ይሻለናል ካልን ተገደን ሳይሆን ጥቅሙን አውቀን ወደንና ፈቅደን እሱ እንደሚበልጥብን ተረድተን መርጠን እንድናመልከው፡፡ ሕይወትን ካላልንና እንደማይጠቅመን እያወቅን ሞትን ኃጢአትን ፍዳን ከመረጥን ደግሞ ይሄንን ምርጫችንን አክብሮልን የመረጥነውን እንድናደርግ እንድንወስድ መብት ሰጥቶናል ሁለቱንም አማራጭ አቅርቦልናል፡፡

እግዚአብሔር ሌላኛውን አማራጭ ሳይሰጥ ሳይፈቅድ ሳያቀርብ ያለ አማራጭ አንድ ምርጫ ብቻ አቅርቦ ወይም ሰጥቶ በዚያ አንድ አማራጭ እሱን ብቻ እንድናመልክ ማድረግንና ማስገደድን ያልፈለገበት ምክንያት እሱ ፍጹም ቅን ፍትሐዊና በነጻ ፈቃድ የሚመለክ እንከን ወቀሳ የሌለበት አምላክ እንጅ አስገድዶ የሚገዛ የሚመለክ አንባገነን አምላክ ስላልሆነ ነው፡፡

ስለሆነም ሁለቱንም አማራጮች እንቢ የማለትንና እሽ የማለትን፣ የሞትንና የሕይዎትን አማራጮች አቀረበልን፡፡ እንደምርጫችንም እንድንሔድ ፈቀደለን ሙብትና ነጻነትን ምርጫውን ለእኛው ሰጠን፡፡ እናም እግዚአብሔር ማንም ተገዶ እንዲገዛለት እንዲያመልከው አይፈልግም፡፡ የተሻለው ምርጫ እሱ መሆኑን አውቆ ወዶት ፈቅዶት መርጦት እንጅ፡፡ አይ ያለንና የሚያስከፍለውንም ዋጋ ለመቀበል ለተዘጋጀው ደግሞ ሲፈልግ እራሱ የቀረጸውን የጥኝ ምስል አምላክ ፈጣሪ ብሎ ከማምለክ ጀምሮ እራሱን እግዚአብሔርን እስከ መዝለፍ ማንቋሸሽ መቃወም ሀልዎቱን ጨርሶ መካድና ማስካድ ድረስ በፈለገው እርኩሰት መርከስ መቆሸሽ ማደፍ መጉደፍ ድረስ ሙብትና ነጻነትን ሰጥቷል፡፡

በዚህም መሠረት ይህ አማራጭ ከቀረበላቸው ሠራዊተ መላእክት አንዱ ሳጥናኤል ነበረና እሱ ግን ከቅንነት ክፋትን፣ ከታዛዥነት አለመታዘዝን፣ ከጽድቅ ኃጢአትን፣ ከበጎነት ዐመፃን ከመምረጥም አልፎ ጭራሽ እንዲያውም ከዚያም አልፎ ከአምላኪነት ተመላኪነትን ሽቶ እግዚአብሔር እንዳልሆነ እያወቀ የእግዚአብሔርን ሥልጣን፣ እግዚአብሔር መሆንን፣ እንደ እግዚአብሔር መከበርን መመለክን ሽቶ በማመፁ ለውድቀት በቃ፡፡ ምርጫው የራሱ ነበርና ከመሰለው ካመነበት ከቅንነት ክፋትን፣ ከታዛዥነት ዐመፃን፣ ከጽድቅ ኃጢአትን የመምረጥ ነጻነትና ሙብት ስለተሰጠው ስለነበረው የመረጠውን ምርጫ ልዑል እግዚአብሔርም አከበረለት፡፡በምርጫው መሠረትም የምርጫውን ውጤት አገኘ ከሥልጣኑ ተሻረ ተዋረደ ተባረረ፡፡

እግዚአብሔር ሰይጣንን ሳይፈጥረው በፊት ሰይጣን ይሄንን የክፋት መንገድ እንደሚመርጥ በሚገባ ያውቃል ፈጣሪ ነውና ከእሱ የሚሠወር ነገር የለምና፡፡ ነገር ግን “ሰይጣን የክፋት መንገድን እንደሚመርጥ አውቃለሁና አልፍጠረው!” ቢል ወይም “ክፋትን እንዳይመርጥ አድርጌ ልፍጠረው!” ቢል ወይም “እኔን የሚመርጡኝን የሚታዘዙልኝን ብቻ ልፍጠር!” ቢል ፍጹም ቅን ፍትሐዊ በነጻነት አስመርጦ ተመላኪ መሆኑ ቀርቶ እሱን የሚወዱትን የሚያመልኩትን ብቻ የሚፈጥር አንባገነን አምላክ ስለሚያደርገውና እሱ ደግሞ እንዲህ ዓይነት አምላክ ስላልሆነ በአምላክነቱ ሰይጣን እንደሚስት እያወቀም ፈጠረው፡፡ ለነጻነትና ለሙብት ታላቅ ሥልጣንን ሰጥቷልና የገዛ ራሱንም ለዚህ ነጻነትና ሙብት ተገዥ አድርጓልና የማይቀለበስ መቸም የማይነፍገው ሁሉም የፈለገውን የመምረጥ ሙብትና ነጻነት ሰጥቷልና፡፡ ስለዚህ ለሰይጣን ሰይጣንነት ተጠያቂው ያዋጣኛል ብሎ ክፋትን አለመታዘዝን ዐመፃን የመረጠው እራሱ ሰይጣን እንጅ ልዑል እግዚአብሔር አይደለም ማለት ነው፡፡

እንግዚብሔር ተጠያቂ ሊሆን ይችል የነበረው ወደፊት ሰይጣን እንደሚክድ እንደሚስት ማወቁ በሰይጣን መሳት ላይ አስተዋጽኦ ጫና ቢያደርግ ቢኖረው ወይም ደግሞ ሰይጣን መጨረሻው መሳት እንደሆነ እግዚአብሔር እንደሚያውቅበት

ቢያውቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም "ምንም ያህል ጽድቅ ብሠራ መጨረሻየ መኮነን ገሃነም መግባት ስለሆነ ምን ሊሠራልኝ ጽድቅን እሠራለሁ!" የሚል ቀቢጸ ተስፋ ሊያሳድርበት ይችላልና፡፡

ወደ ሰው ልጆች ስንመጣም ያለው ነገር ያው ነው፡፡ የሚለየው ነገር ቢኖር ሰይጣን ክፋትን የመረጠው በራሱ ፍላጎት ብቻ ሲሆን ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ የሰው ልጆች እንዲስቱ ግን ከጽድቅ ይልቅ ኃጢአትን ከመታዘዝ ይልቅ ዐመፃን እንድንመርጥ ግን የሰይጣን ምክር ማታለልና ግፊት መኖሩ ጭምር ነው፡፡ ይኼም ሆኖ እኛ የሰው ልጆች የሰይጣንን ክፉ ምክር ግፊትና ማታለል "እንቢ አልቀበልም!" የማለትና ያለመርከስ መብትና ነጻነት ፍላጎትና አቅምም ተሰጥቶናል፡፡ ለሥጋዊ ጥቅሞች እያደላን እንስታለን እንጅ፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ እኛ የሰው ልጆች ከጥቂቶች በስተቀር እግዚአብሔር የሰጠንን አቅምና እውቀት ተጠቅመን የእግዚአብሔርን ኃይል ታጥቀን ያልበደልን መሆን ባንችልም ቅሉ፡፡ ከነዚያ ከጥቂቶች በስተቀር የተቀረነው ግን የሰይጣንን ክፉ ምክሩንና ግፊቱን እንቢ እንዳልን በንጽሕና በቅድስና ጸንተን እንደተፈጠርን ንጹሕ ሆነን መኖር ሳንችል ቀርተናል፡፡ እንዲህ ብየ ስል "እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው" ያዕ.4፤17 ይላልና እንዲህ ስል እኛን በዚህ ደረጃ ለክቶ አይለደም፡፡

እግዚአብሔርም ይኼንን ማለትም ያለብንን ፈታኝ፣ አሳች፣ ክፉ ባለጋራ (ሰይጣን) ብርታት የእኛን የሰው ልጆችንም ድካም ያውቃልና ሽህ ጊዜ ብንጎድፍ ብንወድቅ ብናጠፋ ብንበድል እንደበደላቹህ እንደረከሳቹህ እንደጠፋቹህ ቅሩ ሳይል ከጉድፈታችን ታጥበን የምንነጻበትን፣ ከውድቀታችን እንደገና የምንነሣበትን፣ ከእርኩሰታችን ተፈውሰን የምንቀደስበትን፣ ከስብራታችን የምንጠገንበትን፣ ከመበደላችን እንዳልበደልን የምንሆንበትንና ያዘጋጀልንን ክብሩንና መንግሥቱን የምንወርስበትን ደገኛ ሥርዓት ንስሐን ሠራልን፡፡

ስለሆነም በቃ! ወድቀናል፣ በድለናል፣ ኃጢአት ሠርተናል፣ እረክሰናል፣ ተስፋ የለንም ብለን እንደጠፋን ልንቀር የምንችልበት አንድም ምክንያት የለም፡፡ ሞት ሳይቀድመን ዕድሉን መጠቀም እስከቻልን ጊዜ ድረስ እንዳልበደለና እንደገና ንጹሕ ልንሆን የምንችልበት የንስሐ ሥርዓት አለና፡፡ ይኼ ሰፊ ዕድል እያለን እንደወደቅን እንደረከስን ከቀረን ተጠያቂው እኛው እራሳችን እንሆናለን እንጅ አሁንም ልዑል እግዚአብሔር አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ማንንም ኃጢአተኛ አድርጎ ወይም ኃጢአት እንዲሠራ አድርጎ አይፈጥርምና፡፡ እኛው እራሳችን ለሥጋዊ ተድላ እያደላንና በሰይጣን ምክር ለመታለል እየፈቀድን እንደሆነ ሁሉ ኃጢአት የምንሠራው ተጠያቂዎቹም እራሳችን ነን፡፡ ምርጫው የራሳችን ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በብዙ ሰዎች ዘንድ የሚነገር ከሃይማታዊ አስተምህሮ አንጻር ሲታይ የተሳሳተና በሃይማኖታዊ አስተምህሮ ውስጥ የሌለ ነገር ግን አባባሉ ሃይማኖታዊ የሚመስል አንድ አባባል አለ፡፡ ይህ አባባል ብዙ ባልተማሩ የሃይማት አባቶች ዘንድ ሳይቀር ሲጠቀስ ይሰማል፡፡ እሱ ምንድን ነው? "የእያንዳንዳችን እጣ ፋንታ አስቀድሞ ተጽፏል ከዚያ ከተጻፈልን ውልፍት አንልም የተጻፈልንን ነው የምንኖረው" የሚል አባባል ነው፡፡

ይሄ ግን ያልተማሩ፣ መጽሐፍ የማያውቁ፣ በግምት የሚያወሩ ሰዎች አባባል ነው እንጅ ከቅዱሳት መጻሕፍት ይሄንን የሚል ወይም የሚደግፍ አንድም ቃል የለም፡፡ እርግጥ ነው አንድ ሰው ገና ሳይወለድ ከበዙ ዘመን በፊት ከተወለደ በኋላ ምን እንደሚሠራ የሚናገሩ ትንቢቶች አሉ ለምሳሌ ይሁዳ፡፡ ያሁዳ ገና ሳይፈጠር ከሽህ ዓመታት በፊት ጌታውን አሳልፎ ለሠላሳ ብር እንደሚሸጥ በትንቢት ይነገር የነበረና የሚታወቅ ነው፡፡ ይሄ ማለት ግን ይሁዳ የተፈጠረው ጌታን ለመሸጥ ነው ማለት አይደለም፡፡ ጌታ ሁሉን አዋቂ እንደመሆኑ መጠን ነገሮች ከመፈጸማቸው በፊት አስቀድሞ የሚያውቅ እንደመሆኑ መጠን ይሁዳ ገና ሳይፈጠር በፊት ከተወለደ በኋላ ሊሠራው ያለውን ተወልዶ የሚሠራውን ነገር አስቀድሞ ያውቃልና እሱን ለነቢያቱ ገለጸላቸው እንጅ ይሁዳን እንዲያ እንዲያደርግ አድርጎ ስለፈጠረው አይደለም፡፡

የሆነው ነገር ከላይ እንደገለጽኩት ሰይጣንና እንደሁላችንም በዳዮች ሁሉ ይሁዳም በተሰጠው ነጻነትና ሙብት ነጻ ፈቃድና ፍላጎት ያደረገውን ለማድረግ በመምረጡ ያደረገውን ሁሉ አደረገ፡፡ ለዚህ ለሠራው ጥፋትም ኃላፊነቱን የሚወስደው ተጠያቂው እራሱ ጥፋትን የመረጠው ነው እንጅ ፈጣሪ አይደለም፡፡ እንዳልኩት ይሄንን ይሁዳ ያደረገውን ነገር ግን ጌታ አስቀድሞ ያውቅ ነበር ሁሉን አዋቂ ነውና፡፡ ጌታ ይሄንን በማወቁ ግን እኛ በምንፈጽመው ነገር ላይ የሚያመጣው አንድም ተጽዕኖ የለም፡፡ ሙሉ ለሙሉ ሙብቱና ምርጫው የኛ የራሳችን ነው፡፡

የይሁዳ መጨረሻ እንደታወቀው ሁሉ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ የሁላችንም ከተወለድን ጀምሮ እስክንሞት ድረስ የምናደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነውና በእግዚአብሔር ዘንድ በሚገባ ይታወቃል፡፡ እንደዚያ እንድናደርግና አድርገን እንድናልፍ ግን የእሱ እጅ የለበትም፡፡ ምርጫውና ፍላጎቱ የየግላችን ነው፡፡ ክፉ ነገር ማድረግ እንደሚያስቀጣ ተነግሮን እያወቅን ክፉ ነገር የምናደርግ ከሆነ ባደረግነው ነገር ሁሉ ተጠያቂዎቹ እራሳችን እንጅ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለሆነም "እጣ ፋንታ ነው የተጻፈልንን ነው የምንኖረው" የሚባለው አባባል ልማዳዊ የጨዋ ሰዎች (ያልተማሩ) አባባል እንጅ ትክክለኛ ወይም ሃይማኖታዊ ተቀባይነት ወይም መሠረት ያለው አነጋገር አይደለም፡፡ እዚህ ላይ ግን ሳላነሣው የማላልፈው ነገር ቢኖር ከላይ የገለጽኩት ነገር እንዳለ ሆኖ በአያት በቅድመ አያት ላይ ከዚያም አልፎ እስከ ሽህ ትውልድ ድረስ የተፈጸመ የተደረገ ምርቃት ወይም እርግማን ከተመረቀው ወይም ከተረገመው ሰው ዘር በመወለድ ብቻ የምርቃቱ ወይም የእርግማኑ ተካፋይ የሚኮንበት ሁኔታ እንዳለ ማስታወስ እወዳለሁ፡፡

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስና ከላይ ባየነው መሠረት እግዚአብሔር ማንንም አስገድዶ እንዲያምኑበት አይፈልግም አይፈቅድምም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም "የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም" ዮሐ. 1፤11 ሲል "ኢየሱስ የመጣው ለእስራኤላዊያን ብቻ ነው ወገኖቹም እነሱ ብቻ ናቸው" ማለቱ ሳይሆን ከእነ አብርሃም ጀምሮ ዘፍጥ. 17፤7-28 ለእነ ይስሐቅ ዘፍ. 26፤12-18 ለእነ ያዕቆብ ዘሌ. 26፤42 ለእነ ዳዊት 2ኛ ሳሙ. 7፤12-16 ባጠቃላይ አባቶቻቸው እግዚአብሔርን ፈልጎ ተመራምሮ ከማግኘት ጀምሮ በሠሩት በጎ በጎ የጽድቅ ሥራና ከዚህም የተነሣ በገባላቸው ቃልኪዳን ምክንያት ከሌሎች የሰው ልጅ ነገዶች ወገኖች ተለይተው "የእግዚአብሔር ወገኖች" ለመባል ወይም ለመሆን ችለው ነበርና "የገዛ ወገኖቹ" ሲል ገለጻቸው እንጅ የመጣው የተወለደው ለእነሱ ብቻ ስለሆነ የተቀረውን የሰው ልጅ እሱ ስላልፈጠረ ወይም ለእነሱ ግድ ስለሌለውና ማመን ቢፈልጉም የማይቀበላቸው ስለሆነ አይደለም፡፡

ይሁንና የእስራኤል ልጆች አስቀድሞ ለአባቶቻቸው በገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት ከእነሱ ቢወለድም እግዚአብሔር በውድ እንጅ በግድ እመኑብኝ ተቀበሉኝ አምልኩኝ አይልምና እነሱም መቀበል አልፈለጉምና ሳይቀበሉት ቀሩ፡፡

ማመን በውድ እንጅ በግድ አለመሆኑንና ይመን እንጅ ከእስራኤል ወገን ውጭ የሆነውም የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን መብት እንዳለው ሲያጠይቅ “የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም” የሚለውን ጥቅስ እንዲህ በማለት እዛው ላይ ቀጥሎታል “… ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም” ዮሐ. 1፤12-13

ይሄው ሐዋርያ በመልእክቱም “እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል” 1ኛ ዮሐ.4፤14 ሲል ክርስቶስ ኢየሱስ የመጣው ለዓለሙ ሁሉ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

እሱ ራሱ ክርስቶስም ለሐዋርያቱ “ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ይፈረድበታል” ማር. 16፤15 በማለት የተወለደው ለአባቶቻቸው በገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት “የገዛ ወገኖቹ” ለተባሉት ለእስራኤል ወገኖች ብቻ ሳይሆን ለፍጥረቱ ሁሉ መሆኑን በወንጌሉ ተናግሯል፡፡

እዚህ ላይ ሳይነሣ መታለፍ የሌለበት ነገር ቢኖር በኦሪቱ ዘመን የእግዚአብሔር ወገኖች፣ ልጆች፣ ሕዝብ ይባሉ የነበሩት የእስራኤል ልጆች ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ልጆችም እንደሆኑ አንዳንዴ እንዲያውም ከእነሱም በልጠን የታየን መሆናችን ነው፡፡ ትን. አሞ. 9፤7

ሌላው የሚነሣው ጥያቄ ደግሞ መግቢያዬ ላይ የጠቀስኩት “እግዚአብሔር ለምንድን ነው ከመልካም ነገሮች ጋር አብሮ መጥፎ መጥፎ ነገርን የፈጠረው? አንድ ነገርን ሲፈጥር አብሮ ደግሞ ተቃራኒውን የፈጠረው ለምድን ነው? ለምሳሌ ሁላችንንም ለምን ቆንጆዎች አላደረገንም ለምን ፉንጋንም ፈጠረ?....” የሚለው ነው፡፡ እውነት ነው ብዙ ነገሮችን ያየን እንደሆነ ተቃራኒ ተቃራኒ ነገሮች ላሏቸው፡፡ ለቆንጆ ፉንጋ፣ ለረጅም አጭር፣ ለነጭ ጥቁር፣ ለወፍራም ቀጭን፣ ለጨለማ ብርሃን፣ ለጠንካራ ኮሳሳ፣ ለብልህ ሞኝ፣ ለብልጥ ተላላ፣ ለቅን ክፉ፣ ለጣፋጭ መራራ፣ ለሙቀት ቅዝቃዜ፣ ለቸርነት ንፉግነት፣ ለጭካኔ አዛኝነት፣ ለእሳት ውኃ፣ ለሀብታም ድሀ፣ለውድ ርካሽ እንዲህ እያልን ብዙ መቁጠር እንችላለን፡፡ ያው መቸስ እግዚአብሔር ያለምክንያት ያደረገውና የሚያደርገውም ነገር የለም አይደል? ተቃራኒ ተቃራኒያቸውን ሲፈጥር በምክንያት ነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ ለእያንዳንዱ ነገር በቂና አሳማኝ ምክንያቶች አሉት፡፡ ምክንያቶቹም ማለትም በባሕርያት (ባሕርይ የሚለው ቃል በሥነ ተፈጥሮ ሲወሰድ ተለዋዋጭነት የሌለው ተፈጥሯዊ መገለጫ ነው “ሰው ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ማለትም ከለባዊት ነባቢትና ሕያዊት እንዲሁም ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከእሳት ከውኃ ከአፈርና ከነፋስ የተፈጠረ ነው” እንዲል፡፡ ነገር ግን አንድ ቃል ሦስት አራት ትርጉም የሚይዝበት አጋጣሚ አለና እዚህ ላይ ባሕርይን ከጠባይ ጋር ባለው ተወራራሽ ትርጉም ነው የተጠቀሰው) እናም በባሕርያት ደረጃ ያሉትን ለምሳሌ የክፉነትንና የደግነትን ባሕርያት ሲፈጥር ቀደም ሲል እንዳብራራሁት ሁሉ እንደምርጫችን እንደፍላጎታችን እንሆንባቸው እንድንኖርባቸው ዘንድ ነው፡፡ እግዚአብሔር ማንንም ደግ ወይም ክፉ አድርጎ አይፈጥርም ምርጫውን ለየራሳችን ይተወዋል እንጅ፡፡

እናም እራሳችን በፍላጎታችን የደግነትን ወይም የክፉነትን ባሕርያት እያዳበርን በማደግ የሆነውን እንሆናለን፡፡ የሞኝነት የጅልነትና የመሳሰሉትን ባሕርያት በተመለከተ አሁንም እንግዚአብሔር ማንንም ሞኝ ቂል ጅል ነፈዝ ወፈፌ አድርጎ አይፈጥርም ነገር ግን የሰው ልጆች ባለጋራ ምቀኛ ጠላት ሰይጣን የሰው ልጆችን ለመፈተን በሰው ልጆች ላይ መከራ ለማጽናት በበሽታና በሌሎች ነገሮች እያጠቃ ሰዎችን እንዲህ እንዲሆኑና እግዚአብሔርን እንዲያማርሩ እንዲከዱ እንዲሰናከሉ ጫና ለማሳደር እንዲህ ያደርጋል፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ከላይ እንደገለጽኩት ከተመረቀ ቤተሰብ ከተወለድን ደግና ቅን፤ ከተረገመ ቤተሰብ ከተወለድን ደግሞ ክፉና እርጉም የመሆን ዕድላችን ሰፊ ይሆናል፡፡ ከተረገመ ቤተሰብ መወለዳችንን የምናውቅ ከሆነ በጾም በጸሎት በሥግደት እግዚአብሔርን በመማጸን እርግማኑ በእኛ ላይ እንዳይሠራ እንዳያርፍ ማድረግ የሚቻልበት ዕድልም አለ፡፡

ከዚህና ይሄንን ከመሰሉ ነገሮች ውጪ ያሉ በተፈጥሮ የተደረጉ ለምሳሌ ለውብ ተቃራኒ ፉንጋን፣ ለነጭ ጥቁርን፣ ለብርሃን ጨለማን የመሳሰሉትን ያደረገበት ወይም የፈጠረበት ምክንያት ደግሞ፤ እዚህ ላይ የሁለተኛ ደረጃ የአካባቢን (Habitat) የመጣቅ (Science) ትምህርትን ሀሁ ብጠቅሰው ጥሩ ሊያስረዳን ይችላል፡፡ ሳርና ቅጠል በል (Herbiberes) ሥጋ በል (Carniberes) ሁለቱንም በል (Omniveres) እያሉ ዑደት (Cycle) ሠርተው እንዳስተማሩን ታስታውሳላቹህ፡፡ አንደኛው ለሌላኛው ሕልውና መሠረቱ ነው ወይም አንደኛው ያለ ሌላኛው መኖር አይችልም፡፡ ሳርና ቅጠል ከሌለ ሳርና ቅጠል በል እንስሳት አይኖሩም፡፡ ሳርና ቅጠል በል እንስሳት ከሌሉ ሥጋ በል እንስሳት (አራዊት) አይኖሩም፡፡ እነዚህ ሁለቱም ከሌሉ እንደ ሰው ያለ ሁለቱንም በል ፍጥረት አይኖርም፡፡ አንደኛው በሌላኛው ተደግፎ ነው ህልው የሚሆነው፡፡ ከእነዚህ ከመሀላቸው አንዱ ቢጎድል ሕይዎት አትቀጥልም፡፡ ሁሉም ሲኖሩ ነው ተፈጥሮ ሚዛኗን ጠብቃ መቀጠል የምትችለው፡፡

ይሄንን አስተምህሮ ወደ ኅብረተሰብ ሕይዎትና ኑሮ ስናመጣው ለብልጦች ህልውና የዋሀን አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ሁሉም ሰው ብልጥ ቢሆን ሊፈጠር የሚችለውን ቀውስ አስቡት፡፡ እንደ አራዊት እርስ በእርስ እንባላና እንጠፋፋለን ምድርም ወና ትሆናለች እንጅ ሰላም አይኖርም፡፡ ለሌላውም ህልውና የእሱ ተቃራኒ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ አስቀድሜ እንደነገርኳቹህ በአንድም በሌላም ምክንያት ጨካኞች የሚኖሩ ከሆነ የሩሕሩሆች መኖር የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ሰው ጨካኝ ብቻ ከሆነ አሁንም ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ቀላል ነው፡፡ ተጠፋፍቶ ማለቅ ነው የሚሆነው፡፡

በዚህም መሠረት ለጠንካሮች ደካሞች፣ ለረጅሞች አጭሮች፣ ለወፍራሞች ቀጭኖች፣ ለክፉት ደግነት፣ ለስስት ልግስና፣ ለቁጣ ትዕግስት፣ ለእሳቶች ውኃዎች፣ ለሴቶች ወንዶች፣ ለጨለማ ብርሃን፣ ለጥቁር ነጭ፣ ለፍቅር ጥላቻ፣ ለጣፋጭ መራር እንዲህ እያላቹህ መቀጠል ትችላላቹህ፡፡ ፈጣሪ እንዲህ ያደረገበት ምክንያት ተፈጥሮ ሚዛኗን ጠብቃ እንድትኖር ሕይዎት ሳትቋረጥ እንድትቀጥል ለማድረግ ሲል አድርጎታል፡፡ ለአንደኛው ህልውና የሌላኛው መኖር የግድ አስፈላጊ ስለሆነ፡፡

ተቃራኒ ተቃራኒው ባይኖር ግን ሕይዎት ተመሳሳይ አሰልችና አታካች ቃና የሌላት ከመሆኗም በላይ ስለምትቋረጥ እንዳትቋረጥና አሰልች እንዳትሆን ሲል ነው ይሄንን ያደረገው፡፡ የሰው ልጅ ያወቀ የተመራመረ መስሎት በማያውቀውና ባልገባው ነገር ገብቶ በዚህ ተፈጥሯዊ ቀመር ውስጥ የሥነ ሕይዎት ኪነብጀታ (Bio technology) የዘረመል ምሕንድስና (Genetic engineering) እያለ እጁን ባስገባ ጊዜ ሁሉ ወይም እግዚአብሔር ለተፈጥሯዊ ነገሮች ሁሉ ሚዛኑን ምጠናውንና ስሌቱን ጠብቆ እንዲኖር የሠራለትን ቀመር የሚያዛባ አንዳች ነገር ባደረገ ጊዜ ሁሉ ከሥነ ምኅዳር (Ecology) መቃወስ አንሥቶ እስከ የአየር መዛባት መቃወስና አስፈሪ አስደንጋጭ ያልተጠበቁ ውጤቶች ድረስ ሲከሰቱ መቆየታቸውንና እየተከሰቱም እንደሆነ ችግር መፈጠሩ ሲታወቅም ወደቀደመው ወደ ተነበረበት ቦታ ለመመለስ አቅቶ

ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ገብተን እየቀረን እንደሆነ በዚህም እየተከሰረ እንጅ እየተተረፈ እንዳልሆነ በራሳቸው አንደበት እየተነገረ እየሰማንና ዕያየንም ነው፡፡

እናም ፉንጋ የሆንሽ ሁሉ "እግዚአብሔር ሳይቸግረው ለምን ፉንጋ አድርጎ ፈጠረኝ?" ማለትና "አስፈላጊ አይደለሁም!" ብለሽ ልታስቢ አትችይም አይገባም ማለት ነው፡፡ አላወቅሽውም እንጅ አንችም ደግሞ ቆንጆ ከምትያት የሚበልጥ የራስሽ ጥራት ብቃትና ብልጫ ደግሞ አለሽ፡፡ ምክንያቱም ሚዛኑ ይጠበቅ ዘንድ ይህ መሆኑ ግድ ነውና፡፡

ስለሆነም አላስፈላጊ እንደሆንሽ ልታስቢ አይገባም፡፡ ያለ አንቺ ሚዛኑ አይጠበቅምና እንዲያውም ልትኮሪ ይገባሻል የውቦቹ ውበት እንዲታይ ልብ እንዲባል ያደረግሽላቸው አንቺ ነሽና፡፡ አንቺ ባትኖሪ ኖሮ የውቦቹ ውበት ምንም ይሆን ነበርና አይታወቅም ነበርና፡፡ ሁሉም ተመሳሳዮችና አሰልቺ ይሆኑ ነበርና፡፡ ስለሆነም በሌላ አነጋገር አንቺ የውቦቹ ውበት ነሽ ማለት ነው፡፡

ለሌላውም ነገር ሁሉ ሁኔታው እንደዚሁ ነው፡፡ የፍቅር ጠዓሙና ምንነቱ ይታወቅ ዘንድ የጥላቻ መኖር የግድ አስፈላጊ ሆነ፡፡ ጣፋጩ ማር እንደሚያስፈልገን ሁሉ ኮምጣጣው ሎሚም ያስፈልገናል፡፡ ሌላው ቀርቶ የእባብ መርዝ እንኳን ለባሕላዊም ሆነ ለዘመናዊ መድኃኒት ቅመማ እጅግ አስፈላጊና የማይተካ ጥቅም አለው፡፡ በመሆኑም ስለማናውቀው ስላልደረስንበት እንጅ ያለጥቅምና ያለ አገልግሎት የተፈጠረ ምንም ነገር የለም፡፡ ስንቋጨው እግዚአብሔር ያለ በቂና ያለ አሳማኝ ምክንያት ያደረገው በማድረጉም የተሳሳተው ምንም ነገር ፈጽሞ የለም፡፡ ይሄንን ለመረዳት የአቅምና የዕውቀት ውስንነት ካልገታን ካልገደበን በስተቀር፡፡ "እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ ዐየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ" ዘፍ. 1፤31፡፡ "ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" ሮሜ. 8፤28፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለ ወላዲቱ ድንግል ወለ መስቀሉ ክቡር አሜን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

http://www.ethiopanorama.com